# የቅዱሳን አማላጅነት

ጽድቅን የሚሠሩ ሰዎች በኦሪትና በሐዲስ እንደሚያማልዱ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ተጠቅሷል።

ሀ/ አብርሃም ሚስቱን ሣራን ይዞ ወደ አቤሜሌክ ንጉሥ ጌራራ በተሰደደ ጊዜ መልከ መልካም ስለነበረ ች የዚህ ሀገር ሰዎች አንቺን ሲሉ እንዳይገድሉኝ ወንድሜ ነው በይ እኔም እህቴ ናት እላለሁ አላት እሺ አለች። ከዚያ ሲደርሱ እሱም እህቴ ናት አለ እሷም ወንድሜ ነው አለች።

አቤሜሌክም ከእልፍኙ አግብቶ እደርስባታለሁ ሲል እግዚአብሔር በሕልም መጥቶ ይህች ሴት ባለ ባል ናትና እሷን በመቀማትህ ሞት የተፈረደብህ ነህ አለው። አቤሜሌክም አውቄ አላደረግሁምና ያ ለኃጢአቴ እንደምን ታጠፋኛለህ ? አለው። እግዚአብሔርም መልሶ እኔም ባለማወቅ መሥራትህን አ ውቄ ከመድረስ ከለከልሁህ፣ አሁንም ሴቲቱን ወደባልዋ መልስ፣ እሱም ነቢይ ነውና ስለአንተ ይጸ ልይልህ ትድናለህ፣ ባትመልሳት ግን አንተ እንድትሞት ያንተ የሆነውም ሁሉ እንዲጠፉ እወቅ አለ ው። እዚህ ላይ አቤሜሌክ መጸለይ ሲችል ሳለ እግዚአብሔር አብርሃም ስላንተ ይጸልይልህ ማለቱ ከአቤሜሌክ ጸሎት ይልቅ የአብርሃምን ጸሎት እንደሚቀበል መግለጹ አይደለም? ከዚህ በኋላ አብር ሃም ወደ እግዚአብሔር ጸለየ፣ እግዚአብሔርም አቤሜሌክን ከደዌ ፈወሰው ይላል፤ ዘፍጥረት 20 ፣ 1-18።

ለ/ ኢዮብ ልዩ ልዩ ፈተና ደርሶበት በሕመም ሲሰቃይ በነበረበት ጊዜ አልፋዝ በልዳድ ሳፎር የሚባሉ ወ ዳጆቹ ሊጠይቁት መጥተው በማረጋጋት ፋንታ የሚያሳዝነው ነገር ተናግረው ስለ አሳዘኑት ኋላ ከደዌ ው በፈወሰው ጊዜ እግዚአብሔር ኤልፋዝን «አንተና ሁለቱ ባልጀሮችህ ስለእኔ እንደ ባርያዬ እንደ ኢዮብ ቅንነት አልተናገራችሁምና ቁጣዬ በአንተና በሁለቱ ባልጀሮችህ ላይ ትነዳለች። አሁንም ሰባ ት ወይፈንና ሰባት ዳንግሌ ይዛችሁ ወደ ባርያዬ ወደ ኢዮብ ሂዱና ስለናንተ የሚቃጠል መሥዋዕት አሳርጉ። ኢዮብም ስለእናንተ ይጸልይላችሁ፣ እኔም ጸሎቱን እቀበላለሁ»። ከእዚህ እንደምንረዳው ስለኃጢያታችሁ እግዚአብሔር ወደ እኔ ጸልዩ ከማለት ስለ እናንተ ይጸልይ ነው ያለው። ይህም የኢ ዮብን አማላጅነት ያሳያል። «እግዚአብሔርም የኢዮብን ጸሎት ተቀበለ እግዚአብሔርም ኢዮብ ስለ ወዳጆቹ በጸለየ ጊዜ ምርኮውን መለሰለት» ይላል። ኢዮ. 42፣ 7-11

ሐ/ እሥራኤል አሮንን ፊት ፊታችን እየሄዱ ጠላት የሚያጠፉልን ጣኦታት ሥራልን ብለው ጣዖት አ ሠርተው በሰገዱ ጊዜ፣ ጌታ ተቆጥቶ ሙሴን ተወኝ እኒህን ሰዎች ላጥፋቸውና አንተን በሌላ ሕዝብ ላይ እሾምሀለሁ ቢለው፣ አቤቱ ብዙ ተአምራትን አድርገህ ባሕርን ከፍለህ ጠላት አስጥመህ ባወጣ ኸው ሕዝብ ላይ ጽኑ ፍርድ ለምን ትፈርድበታለህ፣ ይህማ ከሆነ ግብጻውያን ለካስ ከኛ ዘንድ ያወ ጣቸው በምድረ በዳ ሊያጠፋአቸው ኖሯልና ይሉህ የለምን? አቤቱ ከመአት ወደ ምህረት፣ ከቁጣ ወደ ትእግሥት ተመልሰህ ወገኖችህን ይቅር በላቸው፣ ልጆቻችሁን እንደ ሰማይ ኮከብ አበዛላችኋ ለሁ፣ ይህችን ምድር ለዘለዓለም ይወርሳት ዘንድ ለልጆቻችሁ እሰጣለሁ ብለህ የማልክላቸው ባሮች ህ አብርሃምን፣ ይስሐቅን፣ ያዕቆብን አስብ ብሎ ቢጸልይላቸው፣ እግዚአብሔር ከመአት ወደ ምህ ረት፣ ከቁጣ ወደ ትእግስት ተመልሶ ይቅር አላቸው። ያደርግባቸው ዘንድ የተናገረውን ጥፋት አላ ደረገባቸውም «ዘጸአት 32 ፣ 1-15፣ ዘዳግም 9፣12-20 እና 25። «ተወኝ ላጥፋቸው» ብሎ ማማከሩ ባለሟልነቱን፣ አማላጅነቱን ለመግለጽ አይደለም? ልብ አምላክ ዳዊት እንኳን የሙሴን አማላጅነ ት ሲጠቅስ «እንዳያጠፋቸው ቁጣውን ይመልስ ዘንድ የተመረጠው ሙሴ በመቅሰፍት ጊዜ በፊቱ ባ ይቆም ኖሮ ያጠፋቸው ዘንድ ተናገረ» መዝሙር 105(106) ፣23። በፊቱ ባይቆም ኖሮ ሲል ባያማል ዳቸው ኖሮ ለማለት መሆኑ ግልጽ ነው።

መ/ እግዚአብሔር እስራኤልን ከግብጽ በሚያወጣበት ወራት በፈርኦን እንቢተኛነት ጓጉንቸር ባወረደባቸ ው ጊዜ ፈርኦን ሙሴንና አሮንን ጠርቶ ጓጉንቸሩ ይርቅልኝ ዘንድ ወደ እግዚአብሔር ጸልዩልኝ፣ እ ኔም ሕዝቡን ልልቀቅ አላቸው። ሙሴም እሥራኤልን እስከመቼ ትለቀዋለህ ንገረኝና ልጸልይልህ ቢ ለው ጓጉንቸሩ ይልቀቀኝ እንጂ ነገ ይሂዱ አለው። ሙሴና አሮንም ከዚያ ወጥተው ጓጉንቸሩ ይጠ ፉ ዘንድ ወደ እግዚአብሔር አመለከቱ። እግዚአብሔርም ልመናቸውን ሰምቶ ጓጉንቸሩን ከቤትም ከደጅም ከሜዳም አጠፋላቸው ይላል ዘጸአት 8፣ 6-15። ፈርኦን እንኳን በነአሮን አማላጅነት አም ኖ ጸልዩልኝ ብሏቸዋል።

ሠ/ ዳታን አቤሮን በሙሴ ደቂቀ ቆሬ በአሮን ላይ በምቀኝነት በተነሱባቸው ጊዜ እግዚአብሔር ተቆጥቶ ሁሉንም ባንዲት ጊዜ አጠፋቸው ዘንድ ከጉባኤያቸው ፈቀቅ በሉ ቢላቸው ሙሴና አሮን በግንባራ ቸው ተደፍተው ወድቀው አቤቱ አምላክ ሆይ አንተ የሰው ነፍስ አይደለህምን? አንድ ሰው ኃጢአት ሠራ ብለህ በማህበሩ ላይ ለምን ትቆጣለህ ብለው ለምነው ጥፋተኞች ዳታን አቤሮን ደቂቀ ቆሬ ተ

ለይተው ሲጠፉ ሕዝቡን አድነዋቸዋል» ዘኍልቍ16፤ 20-36። በነጋውም የእሥራኤል ልጆች ሁሉ በሙሴና በአሮን ላይ ሕዝቡን አስገደላችሁ ብለው በድንጋይ ሊደበድቡአቸው ተነሱ። ሙሴና አሮንም ወደ ደብተራ ኦሪት ሸሹ። ዓምደ ብርሃን ጋርዶ አዳናቸው። እግዚአብሔርም ሙሴን ከዚህ ከእሥራኤል ፊት ፈቀቅ በሉ፣ እኔ አሁን በቅጽበት አጠፋቸዋለሁ ብሎ ወዲያው መቅሰፍት አምጥቶ ይፈጃቸው ጀመር፣ ወዲያው በአንድ አፍታ 14 ሺህ ከ700 ሰዎች ሞቱ። በዚህ ጊዜ ሙሴና አሮን በግንባራቸው ወድቀው ይጸልዩ ጀመር ሙሴም አሮንን ልብስ ተክህኖ ለብሰህ ማእጠንተ ወርቅ ይዘህ ጸልይላቸው ፤ ኃጢአታቸውን አስተርይላቸው አለው። አሮንም ልብስ ተክህኖውን ለብሶ ማእጠንተ ወርቁን ይዞ በሙታኑና በሕያዋኑ መካከል እየተመላለሰ ቢጸልይላቸው መቅሰፍቱ ፀጥ ብሎላቸዋል፣ ሞት ተከልክሎላቸዋል። ዘኍልቍ 16፤ 41 - 50።

ሰ/ እሥራኤል ተሰብስበው ሄደው ኤርምያስን ጸሎታችን በፊትህ ይድረስ፣ ለእኛም ወደ አምላክህ ወደ እግዚአብሔር ጸልይልን፣ አይንህ እንደሚያየን ከብዙ ጥቂት ቀርተናልና ቢሉት እሺ ወደ አምላካችሁ ወደ እግዚአብሔር እጸልይላችኋለሁ፣ እግዚአብሔርም የሚሰጣችሁን መልስ አልደብቃችሁም እነግራችኋለሁ ብሏቸው እስከ 10 ቀን ከጸለየላቸው በኋላ የእግዚአብሔር ነገር ወደ ኤርምያስ መጣ፣ ከአስር ቀን በኋላ ሕዝቡን ሰብስቦ ጸሎታች ሁን በፊቱ አቀርብ ዘንድ ወደርሱ የላካችሁኝ እግዚአብሔር የእሥራኤል አምላክ በዚህ ምድር ብትቀመጡ እሰራችኋለሁ፣ አላፈርሳችሁም፣ እተክላችኋለሁ አልነቅላችሁም። እናንተ በሰራችሁት ኃጢአት ከደነገጣችሁበት እኔም ባደረግሁባችሁ ክፋት እጸጸታለሁና ከባቢሎን ንጉሥ ፊት አትፍሩ አላችሁ እግዚአብሔር ብሎ ነግሯቸዋልኤር. 42፤ 2 - 13። እንግዲህ እራሳቸው ወደ እግዚአብሔር መጸለይ እየቻሉ ለምን ኤርምያስን ወደ እግዚአብሔርን ጸልይልን አሉት? እግዚአብሔር የኤርምያስ አምላክ ብቻ ነው? « እኔ መንገድና እውነት፣ ሕይወትም ነኝ፣ በእኔ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም» ዮሐ. 14፤6 የሚለውን በመጥቀስ ጌታን አማላጅ አድርገው የሚያቀርቡና ቅዱሳንን ደግሞ እንደማንኛውም ተራ ሰው አድርገው የሚያቀርቡ ብዙ ሰዎች አሉ። በእርግጥ እነኝህ ሰዎች በጣም ተሳስተዋል። እኔ በቀጥታ ወደ ጌታ ፊት ለመቅረብ ብቁ ነኝ የሚል የትዕቢት አስተሳሰብም ያላቸው አሉ። እነዚህ ሰዎች የዲያብሎስ ገንዘብ የሆነችውን ትዕቢት በመያዛቸው በእግዚአብሔር ፊት የከበሩትን ቅዱሳን ያቃልላሉ። ነገር ግን እኔ በቀጥታ ወደ ጌታ ፊት ለመቅረብ ብቁ አይደለሁም በኃጢአት ባሕር የምዋኝ ነኝ ብሎ እግዚአብሔር ባከበራቸው መላእክትና ቅዱሳን አማካይነት መጸለይ ትህትናን ወንድማዊ ፍቅርን ያመለክታል። እንዲሁም የመጽሐፍ ቅዱስን ቃል በትክክለኛ መንገድ መፈጸምን ያሳያል እንጂ አያስነቅፍም።

ከላይ የተጠቀሱት የአማላጅነት ጥቅሶች ከብሉይ ኪዳን ብቻ ናቸው እንዳይባል በሐዲስ ኪዳንም የምልጃ ትምህርት ስለተጠቀሰ እንመለከታለን። « በእኔ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም» ማለት ....እኔን ( በእኔ የባሕርይ አምላአክነት) ያላመነ አብን ሊያምን አይችልም አብም ሊቀበለው አይችልም ማለት ነው እንጂ ቅዱሳን ሊያማልዱ አይችሉም ማለት አይደለም።

በመሠረቱ ጌታ በአማናዊ ቃሉ እንደተናገረው «እኔ ሕግንና ነቢያትን ለመሻር የመጣሁ አይምሰላችሁ ልፈጽም እንጂ ለመሻር አልመጣሁም» ማቴ. 5፤17። እንግዲህ ባለቤቱ ራሱ በኦሪት ያሉት ሁሉም ሕጐች እንዳልተሻሩ እየገለጠልን አንዳንድ አሣሣቾች የሚሉት ቢያጡ ምልጃ በብሉይ ጊዜ ነበር፣ በሐዲስ ግን የምልጃን ሥራ የሚሠራው ጌታ ብቻ እያሉ የባሕርይ አምላክ በሆነውና ተማላጅ በሆነው አምላክ ላይ የማይገባ ነገር ይናገራሉ። እኛ ግን አማላጅነት የፍጡር ሥራ እንጂ የፈጣሪ ሥራ አለመሆኑን እየገለጽን እንዲሁም በሐዲስ ኪዳንም ከተጠቀሱት የቅዱሳንን አማላጅነት አጠር መጠን ባለ ሁኔታ እንገልጻለን።

ሀ/ «እናንተን የሚቀበል እኔን ይቀበላል፣ ነቢይን በነቢይ ስም የሚቀበል የነቢይን ዋጋ ይወስዳል፣ ጻድቅንም በጻድቅ ስም የሚቀበል የጻድቁን ዋጋ ይወስዳል።ማንም ከእነዚህ ከታናናሾቹ ለአንድ ቀዝቃዛ ጽዋ ውኃ ብቻ በደቀ መዝሙር ስም የሚያጠጣ እውነት እላችሀለሁ ዋጋው አይጠፋበትም» ማቴዎስ 10፤40 - 42።

ለ/ የያዕቆብ መልዕክት ምዕ. 5 ቁ 14 - 19 የቅዱሳን ጸሎት በሥራዋ እጅግ ታላቅ ኃይል እንደምታደርግ ይገልጻል። እንዲሁም የካህናት ፀሎት (አማላጅነት) ከሥጋ ደዌና ከኃጢአት ደዌ እንደሚፈውስ ይገልጻል።

ሐ/ የማቴዎስ ወንጌል 15፤ 21 - 28 ባለው ላይ የሐዋርያትን አማላጅነት ያሳያል። ጌታ ከነዓናዊት የሆነችው ሴት « ጌታ ሆይ ማረኝ ልጄን ጋኔን ክፉኛ ይዞታል» ብላ ስትጮህ ምንም መልስ አልመለሰላትም ነበር። ደቀ መዛሙርቱ ቀርበው «በኋላችን ትጮሃለችና አሰናብታት» እያሉ ሲለምኑት ከእርስዋ ጋር የቃል ምልልስ ሊያደርግ ተገዶአል። የሴትዮዋ እምነት ብቻ አይደለም ልጅዋን ከደዌው ሊያስፈውስላት የቻለው፣ የሐዋርያትም አማላጅነት እንጂ።

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እግዚአብሔር ለወዳጆቹ ቃል ኪዳን እንደገባ የሚገልጽ አለ፣ ለምሳሌ መዝሙር 88 (89) ፤3 «ከመረጥሁት ጋን ቃል ኪዳኔን አደረግሁ» በሌላ በኩል በመጽሐፈ ነህምያ 1፤4-7 «...አ

ቤቱ የሰማይ አምላክ ሆይ ለሚወዱህና ትእዛዝህን ለሚያደርጉ ቃል ኪዳንንና ምህረትን የምትጠብቅ እያ ለ እግዚአብሔር ለወዳጆቹ የገባውን ቃል ኪዳን እንደማያጥፍ ያስረዳናል።

እንዲያውም ባይገርማችሁ ቅዱሳን የጸጋ አማልክት ይባላሉ። ይህም ማለት እግዚአብሔር እርሱ የሚሠ ራውን ሥራ ሁሉ እነሱ እንዲሠሩ አድርጎአቸዋል። ይህንንም በመጽሐፍ ቅዱስ ማስረጃነት አስደግፌን ማቅረብ እንችላለን።

– **<u>ዘጸአት</u>** <u>7፤1</u> «እግዚአብሔር ሙሴን አለው፣ እይ እኔ ለፈርኦን አምላክ አድርጌሃለሁ ወንድምህም አሮ ን ነብይ ይሆንልሃል» ይህ ማለት እግዚአብሔር ሙሴ ታላላቅ ድንቅ ተአምራትን ያደርግ ዘንድ የጸጋ አ ምላክ ሆኖ መሾሙን የሚያስገነዝበን ነው።

– **<u>መዝሙር</u>** <u>81(82) ፤1 - 8</u> «እግዚአብሔር በአማልክት ማህበር ቆመ፣ በአማልክትም መካከል ይፈርዳ ል፣...እኔ ግን አማልክት ናችሁ ሁላችሁም የልዑል ልጆች ናችሁ ነገር ግን እንደ ሰው ትሞታላችሁ፣ ከ አለቆችም እንደ አንዱ ትወድቃላችሁ አልሁ።» እንግዲህ እኔ አማልክት ናችሁ አልሁ ብሎ የአምላክነ ትን ሥልጣን የሰጠው ለነማን ነው? ለቅዱሳን አይደለምን?። ይህንን ልናብል አንችልም፤ ቃሉም ሊሻር እንደማይችል «እኔ አማልክት ናችሁ አልሁ ተብሎ በሕጋችሁ የተጻፈ አይደለምን? መጽሐፉ ሊሻር አይ ችልምና እነዚያን የእግዚአብሔር ቃል የመጣላቸውን አማልክት ካላቸው...» ዮሐንስ ወንጌል 10፤34 ብ ሎ የቅዱሳንን ዘለዓለማዊ አማላጅነት ያረጋግጥልናል። እንግዲህ በዚያን ጊዜ ሁሉም በአግረ አጋንንት እ የተጠቀጠቀ ጽድቃችን እንደ መርገም ጨርቅ ሆነ ይሉ በነበረበት ወቅት የጸጋ አምላክነት ከተሰጣቸው፣ ዛሬ በክርስቶስ ካሳ ከማህበረ መላእክት ከተጨመሩ በኋላ «እኛ በክርስቶስ ፈንታ ክርስቶስን መስለን እ ንደ ክርስቶስ እንለምናለን» 2ኛ ቆሮ. 5፤20 ለማለት የበቁት የሐዲስ ኪዳን ጻድቃንማ ምን ያህል አይከ ብሩ? እነሱም የጸጋ አማልክት ይባላሉ። ለማማለድም የሚያግዳቸው ምንም ነገር የለም» እውነት እውነ ት እላችኋለሁ በእኔ የሚያምን እኔ የማደርገውን ሥራ እርሱ ደግሞ ያደርጋል፣ ከዚህም የሚበልጥ ያደ ርጋል ዮሐንስ ወንጌል 14፤12 እንግዲህ የቅዱሳን አማላጅነት ብርቅ ድንቅ ሆኖ በመጽሐፍ ቅዱስ ያልሰ ፈረ ነው ተብሎ የሚነገረው ለምንድን ነው? እራሱ ጌታ እኔ ካደረግኩት የበለጠ ያደርጋሉ ብሎ እየመሰ ከረ። እሱ የአራት ቀን ሬሳ አልዓዛርን አነሳ፣ እነቅዱስ ጊዮርጊስ ደግሞ ከሞቱ ዘለግ ያለ ጊዜ የሆናቸው ን ሙታን በክርስቶስ ስም አስነሱ። አይችሉም እንዳንል ራሱ ባለቤቱ ከእኔ የበለጠ ያደርጋሉ ብሎ አስ ረድቶናል።

እንዲያውም ይድነቃቸውና ቅዱሳን እንኳን ማማለድ ይፈርዳሉ። ሁሉንም ነገር ለማድረግ ይችላሉ፣ የ ሚሳናቸው ነገር የለም «የሰናፍጭ ቅንጣት ታህል እምነት ቢኖራችሁ ይህንን ተራራ ከዚህ ወደዚያ እለፍ ብትሉት ያልፋል የሚሳናችሁም የለም» ማቴ. 17.19 አያማልዱም፣ የእኛና ጉዳይ ሊያስፈጽሙ አይች ሉም ከተባሉ የጌታ ቃል ተፈጻሚነቱ ምኑ ላይ ነው?ጌታ ደግሞ የእውነት አምላክ ነው።ውሸቱን ሁሉንም እፈጽምላችኋለሁ ብሎ ኋላ አልፈጽምም አይልም። ጌታ በማቴ. 5፤14 «እኔ የዓለም ብርሃን ነኝ» ብሏ ል። በዮሐንስ ወንጌል 9፤12 ላይ ደግሞ ሐዋርያት « የዓለም ብርሃን ናችሁ» ተብለዋል፣ አማልደው ከ ጌታ ጋር ካላገናኙን የዓለም ብርሃንነታቸው ምኑ ላይ ነው?

እንኳን ለክርስቶስ ወንጌል የታመኑት እስከ ፍጻሜ ሕይወታቸው ለቃሉ ምስክር የሆኑት ሰማእታት፣ ሐዋር ያት ጻድቃን ቀርተው ጌታ በዚህች ምድር ላይ በሥጋ ይመላለስ በነበረበት ጊዜ ብዙ ሰዎች ሌሎችን አማልደው ድህነተ ሥጋ አሰጥተዋቸዋል። አባት ለልጁ በመለመን፣ እናት ለልጅዋ በመለመን ዘመድ ለዘ መዱ በማማለድ፣ ብዙዎች ከጌታ ዘንድ ለወገኖቻቸው ፈውስ አሰጥተዋል። መጽሐፍ ቅዱስ አሁንም ይ ህን ለመመስከር ዝግጁ ነው።

ወደ ቅፍርናሆም በገባ ጊዜ የመቶ አለቃ ወደ እርሱ ቀርቦ «ጌታ ሆይ ብላቴናዬ ሽባ ሆኖ እጅግ እየተሰ ቃየ በቤት ተኝቶብኛል» ብሎ ለመነው። ኢየሱስም «እኔ መጥቼ እፈውሰዋለሁ አለው፣ የመቶ አለቃው ም መልሶ ጌታ ሆይ በቤቴ ጣራ በታች ልትገባ አይገባኝም፣ ነገር ግን በቃልህ እዘዝ እንጂ ብላቴናዬ ም ይፈወሳል። ኢየሱስም ሰምቶ ተደነቀና ለተከተሉት እንዲህ አለ፣ «እንዲህ ያለ ትልቅ እምነት አላገ ኘሁም» ማቴ 8፤10።

– እነሆም በአልጋ የተኛ ሽባ ወደ እርሱ አመጡ፣ ኢየሱስም እምነታቸውን አይቶ ሽባውን «አንተ ልጅ አይዞህ ኃጢአትህ ተሰረየችልህ» አለው። .....ተነሳ አልጋህን ተሸክመህ ወደ ቤትህ ሂድ አለው፣ ማ ቴዎስ 9፤26።

–ይህንንም ሲነግራቸው አንድ መኮንን መጥቶ፣ ልጄ አሁን ሞተች ነገር ግን መጥተህ እጅህን ጫንባት በሕይወትም ትኖራለች» እያለ ሰገደለት ማቴዎስ 9፤18።

– ወደ ሕዝቡም ሲደርሱ አንድ ሰው ቀረበና ተንበርክኮ «ጌታ ሆይ ልጄን ማርልኝ በጨረቃ እየተነሳበት ክፉኛ ይሰቃያልና ብዙ ጊዜ በእሳት ብዙ ጊዜም በውኃ ይወድቃልና ወደ ደቀመዛሙርትህም አመጣሁ ት፣ሊፈውሱትም አቃታቸው አለው፤ ማቴ. 17:14

– እነሆም ከነአናዊት ሴት ከዚያ አገር ወጥታ ጌታ ሆይ የዳዊት ልጅ ማረኝ፣ ልጄን ጋኔን ክፉኛ ይዞአ ታል፣ ብላ ጮኸች። እርሱ ግን አንዳችም አልመለሰላትም፣ ደቀመዛሙርቱም ቀርበው « በኋላችን ት ጮሃለችና አሰናብታት» እያሉ ለመኑት፣ እርሱም መልሶ «ከእሥራኤል ቤት ለጠፉት በጎች በቀር አልተ ላክሁም» አለ። እርስዋ ግን ወጥታ «ጌታ ሆይ እርዳኝ» እያለች ሰገደችለት፣ እርሱ ግን መልሶ « የል ጆችን ይዞ ለቡችሎች መጣል አይገባም» አለ፤ እርስዋም «አዎን ጌታ ሆይ ቡችሎች እኮ ከጌቶቻቸው ማእድ የወደቀውን ፍርፋሪ ይበላሉ» አለች። በዚህ ጊዜ ኢየሱስ «አንቺ ሴት እምነትሽ ታላቅ ነው፣ እ ንደወደድሽ ይሁንልሽ» አላት። ልጅዋም ከዚያች ሰዓት ጀምሮ ዳነች፣ ማቴዎስ፣15: 22 - 29።

– አራት ሰዎችም የተሸከሙትን ሽባ አመጡለት፣ ስለሕዝቡም ብዛት ወደእርሱ ማቅረብ ቢያቅታቸው እርሱ ያለበትን የቤቱን ጣራ አነሱ፣ ቀጥለውም ሽባው የተኛበትን አልጋ አወረዱ ኢየሱስም እምነታቸው ን አይቶ ሽባውን « አንተ ልጅ ኃጢአትህ ተሰረየችልህ» አለው ማርቆስ 2፣3።

– ኢየሱስም ደግሞ ወደ ማዶ ከተሻገረ በኋላ. . . . ኢያኤሮስ የተባለ ከምኩራብ አለቆች አንዱ መጣ፣ ባየውም ጊዜ በእግሩ ላየ ወደቀና «ታናሽቱ ልጄ ልትሞት ቀርባለችና እንድትድንና በሕይወት እንድትኖር እጅህን ጫንባት» ብሎ አጥብቆ ለመነው፣ ማር. 5: 22።

– ታናሺቱ ልጅዋ ርኩስ መንፈስ ያደረባት አንዲት ሴት ስለእርሱ ሰምታ መጣችና በእግሩ ላይ ተደፋች ፣. . .ከልጅዋም ጋኔን ያወጣላት ዘንድ ለመነችው. . . ስለዚህ ቃልሽ ሂጂ ጋኔኑ ከልጅሽ ወጥቶአል አላ ት። ወደ ቤቷም ሄዳ ጋኔኑ ወጥቶ ልጅዋም በአልጋ ላይ ተኝታ አገኘች፣ ማርቆስ 7: 25 - 29።

– ወደ ቤተ ሳይዳም መጡ። እውርም አመጡለት፤ እንዲዳስሰውም ለመኑት፣ እውሩንም እጁን ይዞ ከ መንደር ውጭ አወጣው፣ በዓይኑም ተፍቶበት እጁንም ጭኖበት አንዳች ታያለህን? ብሎ ጠየቀው፣ አሻ ቅቦም ሰዎች እንደ ዛፍ ሲመላለሱ አያለሁ አለ። ማር. 8: 22 - 23።

– ከሕዝቡ አንዱ መልሶ መምህር ሆይ ዲዳ መንፈስ ያደረበትን ልጄን ወደ አንተ አምጥቼዋለሁ፣ በያዘ ውም ስፍራ ሁሉ ይጥለዋል። አረፋም ይደፍቃል፣ ጥርሱንም ያፋጫል፣ ያደርቃልም፣ እንዲያወጡለት ም ለደቀመዛሙርትህ ነገርኳቸው፣ አልቻሉም አለው፣ ማር. 7: 17።

– እነሆም አንድ ሽባ በአልጋ ተሸክመው አመጡ፣አግብተውም በፊቱ ሊያኖሩት ይሹ ነበር፣ስለ ሕዝቡ ም ብዛት እንዴት አድርገው እንዲያገቡት ሲያቅታቸው ወደሰገነቱ ወጡ፣የጣራውንም ጡብ አሳልፈው በመካከል በኢየሱስ ፊት ከአልጋው አወረዱት እምነታቸውንም አይቶ «አንተ ሰው ኃጢአትህ ተሰረየች ልህ» አለው፣ ሉቃስ 5: 18 - 20።

– እነሆም ከሕዝቡ አንድ ሰው እንዲህ እያለ ጮኸ «መምህር ሆይ ለእኔ ያለኝ አንድ ልጅ ነውና ልጄ ን እንድታድንልኝ እለምንሃለሁ» ሉቃስ 5፣18።

– አንድ የመቶ አለቃም ነበረ፣ የሚወደው ባርያው ታሞ ሊሞት ቀርቦ ነበር። ስለኢየሱስም በሰማ ጊዜ የአይሁድን ሽማግሌዎች ወደ እርሱ ላከና መጥቶ ባርያውን እንዲያድን ለመነው፣ ሉቃስ 7፣2።

– እርሱም ኢየሱስ ከይሁዳ ወደ ገሊላ እንደመጣ ሰምቶ ልጁ ሊሞት ስላለው ወደ እርሱ ሄደ፣ ወርዶ ም እንዲፈውስለት ለመነው፣ ዮሐ. 4፡ 46።

– ማርታ ኢየሱስ እንደመጣ በሰማች ጊዜ ልትቀበለው መጣች፣ ማርያም ግን በቤት ተቀምጣ ነበር። ማ ርታም ኢየሱስን «ጌታ ሆይ አንተ በዚህ ኖረህ ብትሆን ወንድሜ ባልሞተ ነበር፣አሁንም ከእግዚአብሔር የምትለምነውን ሁሉ እግዚአብሔር እንዲሰጥህ አውቃለሁ» አለችው። ኢየሱስም «ወንድምሽ ይነሳል » አላት፣ ዮሐ 11፡ 21 - 24።

– በኢዮጴም ጣቢታ የሚሉአት አንዲት ደቀ መዝሙር ነበረች፣ ትርጓሜው ዶርቃ ማለት ነው። እርስዋ ም መልካም ነገር የሞላበት ምጽዋትም የምታደርግ ነበረች። በዚያም ወራት ታመመችና ሞተች፣ አጥበ ውም በሰገነት አኖሩአት። ልዳ ለኢዮጴ ቅርብ ናትና ደቀ መዛሙርት ጴጥሮስ በዚያ እንዳለ ሰምተው ወ ደ እነርሱ ከመምጣት እንዳይዘገይ እየለመኑ ሁለት ሰዎች ወደ እርሱ ላኩ። «. . .ጣቢታ ሆይ ተነሽ» አላት፣ እርሰዋም አይኖችዋን ከፈተች። ጴጥሮስንም ባየች ጊዜ ተቀመጠች፣ የሐዋ. ሥራ 9፡ 36 - 40።

አሳሳቾች ማወናበድ ልማዳቸው ነውና ቀደም ተብሎ የተጠቀሰውን የሚመስል ብዙ ማስረጃዎች ከመጽ ሐፍ ቅዱስ ሲገኝባቸው ክህደታቸውን ቀየር አድርገው ቅዱሳን በምድር ላይ በሕይወተ ሥጋ እያሉ ያማ ልዱ ነበር። ከሞቱ በኋላ ግን አያማልዱም ይላሉ። ግን ምልጃ በአጸደ ነፍስ ማለት ቅዱሳን ከዚህች አ ለም ወደ እዚያችኛዋ በሞት ከተላለፉም በኋላ ማማለድ እንደሚችሉ አሁንም በቅዱስ መጽሐፍ የተረጋ ገጠ ነው።

በመሠረቱ ይህንን ለማወቅ አስቀድሞ የሰውን ተፈጠሮ መርምሮ ማወቅ ያስፈልጋል። ከአራቱ ባሕርያት ለተፈጠረ ሥጋ የሚያንቀሳቅሱት ደማዊት ነፍስና ነባቢት ነፍስ አሉት። በአፀደ ሥጋ ስለ ደማዊት ነፍስ

የምትሰለጥንበት ስለሆነ በሥራው ሁሉ እናስሳትን መስሎ እንዲኖር በአፀደ ነፍስም ዓለሙ ዓለመ መላእ ክት ሲሆን በአካለ ነፍስ መላእክትን መስሎ ይኖራል። ይህንንም ጌታ ሲገልጽ «በሰማይ እግዚአብሔርን እንደሚያገለግሉ መላእክት ይሆናሉ።» ብሎአል፣ ማቴዎስ 22፥ 27 - 30።

ከትንሣኤ አስቀድሞ ያለውም ዘመን በዓለም ሥጋም ቢሆን በዓለመ ነፍስም ቢሆን የሥራ ዘመን ነው እን ጂ የዕረፍት ጊዜ አይደለም። ይህንንም ቅዱስ ጳውሎስ ሲገልጽ « መላእክት ሁሉ ረቂቃን ሲሆኑ የዘለዓ ለምን ሕይወት ይወርሱ ዘንድ ስላላቸው ለተልእኮ ይላካሉ» ብሏል፣ ዕብራውያን 1፥ 14።

ስለዚህ ጊዜው የሥራ ጊዜ ስለሆነ ዓለሙም ሥራ የሚሠራበት ዓለም ስለሆነ መላእክትና ጻድቃን አንድነ ት ሆነው በዓለመ ነፍስ በአፀደ ሥጋ ላሉት ለበጎዎቹ ይጸልዩላቸዋል። (ያማልዱላቸዋል) በክፉዎች ይጸል ዩባቸዋል።

ማስረጃ፥ የዮሐንስ ራእይ 6፥ 9 - 11 «አምስተኛውን ቁልፍ በከፈተ ጊዜ ከመሰዊያው በታች ሕጉን ስለ ጠበቁ ስለ እግዚአብሔር ቃል የሞቱትን ሰዎች ነፍስ አየሁ፣ እነሱም እውነተኛ የባሕርይ አምላክ አቤቱ ደማችንን በግፍ ያፈሰሱትን ሰዎች በምድር ከሚኖሩ ሰዎች ለይተህ አትበቀላቸውምን አትፈርድባቸው ምን? እስከመቼ ድረስ ትታገሳቸዋለህ? እያሉ በታላቅ ድምጽ ጮሁ፣ ለእያንዳንዳቸውም ብሩህ ብሩህ ል ብስ ሰጥተው እንደ እነርሱ በሰማዕትነት ይሞቱ ዘንድ ያላቸው ወንድሞቻቸው ምእመናን በሰማዕትነት እ ስኪፈጽሙ ድረስ ይታገሱ ዘንድ ትንሽ ቆዩ አሏቸው።»

ይህ የሚያሳየን ከሞት በኋላ መጸለይ እንደሚቻል አይደለምን? በክፉዎቹ ላይ ከጸለዩባቸው ለበጎዎቹ ደግ ሞ እንደሚጸልዩላቸው የታመነ ነው። መናገር አይችሉም የሚሆነውን አያውቁምና፥ ከሞቱ በኋላ አያማ ልዱም ማለት ግን «እኔ የሕያዋን የአብርሃም የይስሐቅ አምላክ ነኝ እንጂ የሙታን አምላክ አይ ደለሁም» ማርቆስ 12፥ 26፣ ያለውን አለማስታወስ ነው። አብርሃምና ይስሐቅ ብለህ እያሉ እነሙሴ ይለ ምኑት የነበረው የሞቱትን ባለሟሎቹን ቃል ኪዳን በሕይወተ ሥጋ እያሉ ብቻ ነው የምጠብቀው መቼ አላቸው? እንዲያውም በሠሩት የጽድቅ ሥራ ሕያዋን እንጂ ሙታን አለመሆናቸውን ገለጸ እንጂ።

በአፀደ ነፍስ መተዋወቅ መነጋገር መጸለይ እንደሚቻል አሁንም ባለቤቱ ራሱ በሉቃስ 16፥ 19 - 31 ባለ ው ላይ ግልጽ አድርጎ አስታውቆናል። ሀብታሙ ሰው አብርሃምን ማረኝ ማለቱ ምንን ያመለክተናል? የአ ብርሃምን የአማላጅነት ሥልጣን መቀበል አይደል? አብርሃም ሀብታሙን ሰውዬ አላነጋገረውም? በአብርሃ ም አማላጅነትስ የሚያምኑትን ሰዎች መላእክት በአብርሃም እቅፍ እንደሚያኖሩአቸው ይገልጽ የለም? ።

በ2ኛ ነገሥት 13፥ 20 ላይ ኤልሳ ከሞተ በኋላ ነፍስ የተለየው አጥንቱ የአንድ ምውት ሬሣ እንዳስነሳ መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል። ቅዱሳን እንኳን በነፍስ በሥጋቸው፣ እንኳን አማልደው፣ ሙትን ያስነሳሉ።እ ንግዲያው የኤልሳ አጥንቱ ሙት ካስነሳ በአማልጅነቱ ተማምነን ከኃጢአት ሞት እግዚአብሔር እንዲያ ድነን ጸልይልን፣ አማልደን ብንለው ይህን ወደ እግዚአብሔር አቅርቦ እያስደርግልን ይሆን? እንመን ያለ ምንም ጥርጥር እንድናለን። ይህ ጸጋ ለኤልሳ ብቻ የተሰጠ ሳይሆን ኤልሳዕን ለመሰሉ ቅዱሳን ሁሉ የተሰ ጠ ጸጋ ነው።

ቅዱሳን እንካን መለመንና ማስደረግ ቀርቶ በዓለሙ ላይ ሁሉ እንዲፈርዱ ጌታ እንዲህ ሲል ይናገራል፥« እውነት እላችኋለሁ እናንተስ የተከተላችሁኝ በዳግመኛ ልደት የሰው ልጅ በክብሩ ዙፋን በሚቀመጥበት ጊዜ እናንት ደግሞ በአሥራ ሁለቱ የእስራኤል ነገድ ልትፈርዱ በአሥራ ሁለት ዙፋን ትቀመጣላችሁ» ማቴዎስ 19፥ 28 - 29።

እንግዲህ ምን እንላለን፣ ባለቤቱ ራሱ ፈራጅ ሲያደርቸው፣ እኛ አይሆንም ፍጡራን ናቸው ስለሆነም በ ፍጡር ላይ ሊፈርዱ አይችሉም ልንል መብት አለን? አንችልም። እግዚአብሔር ያከበረውን ማንም ሊያ ዋርድ አይችልም።

ቅዱስ ጳውሎስ ይህንን የጌታ አማናዊ ቃል መሰረት በማድረግ «ቅዱሳን በዓለም ላይ እንዲፈርዱ አታው ቁምን» ይለናል፣ 1ኛ ቆሮንቶስ 6፥ 2። ጌታ መፍረድ ሰጥቶአቸው ከፍርድ ያነሰውን ማማለድ ከለከላቸ ውን? አይደለም። እነሆ ዛሬ ቅዱሳን በእግዚአብሔር አገር በደስታ አሉ። በምድር ላይ እንደወርቅ በእሳ ት ተፈተነው አልፈዋልና እነሆ ቅዱሳን ዛሬ ስለእኛ ወደ አምላካቸውና አምላካችን ሌት ተቀን ይጮሃሉ ። የጽድቅ ሥራቸው የመጨረሻ ውጤት አፈር ትቢያ ሆኖ መቅረት እንዳልሆነ እናምናለንና አማልዱን፥ እርዱን፥ተራዱን፥ ባላጋራችን ዲያብሎስ እንደ ተራበ አንበሳ አፉን ከፍቶ ሊውጠን እየተንቆራጠጠ ነው ።ዲያብሎስ ብዙ ሠራዊቶቹን አሰማርቶ ከአንዲቱ ሃይማኖት ሊያስወጣን ነው፣ ከነናችን ሆናችሁ አስተ ምሩን፣ምሩን እንላቸዋለን። በክብሩ ዙፋን ዙሪያ የቆማችሁ ቅዱሳን ስለእኛ ወደ ኃያሉ ፈጣሪያችን አማ ልዱ አሜን!

**ዓምደ ብርሃን ከሚለው መጻሕፍ ብርሃኑ ጎበና በ1985 ካሳተሙት የተወሰደ።**